መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን



Kidst Slassie Ethiopian Orthodox Tewahido Church



የመልእክት ሳጥን ቁጥር ፡ P.O. Box 42204 Arlington, VA 22204 (703) 606-1976

## ሳምንታዊ አገልግሎቶቻችን

1. ዘወትር ማክሰኞ፤ ከ6-8p.m. የልጆች ትምህርት፤ ጸሎተ ሰርክ፤ ምህላ፤ ትምህርት…በ5901 Leesburg pike, Falls Church, VA 22041 (በትልቁ ቤተ ክርስቲያን)
2. ዘወትር ቅዳሜ፤ ከ6-10 a.m. ቅዳሴ፤ ትምህርተ ወንጌል፤ መዝሙር….በ5150 Leesburg pike Alexandria, Virginia 22302 (በትንሿ ቤተ ክርስቲያን)
3. ዘወትር እሁድ፤ ከ6፡00-10:00 a.m. ቅዳሴ፤ ትምህርተ ወንጌል፤ መዝሙር…(በ5901 Leesburg pike, Falls Church, VA 22041 (በትልቁ ቤተ ክርስቲያን)
4. የቴሌቪዥን መርሃ ግብር፡ ረቡዕ 8-9 p.m.፣ ቅዳሜ ከ3-4p.m.፣ እሁድ ከ5-6p.m. በቻናል 30…እንደየ ኬብል ካምፓኒው ሊለያይ ይችላል።

# ከክፉ ነገር ሁሉ የሚጠበቁበት ጸሎት

## የዳዊት መዝሙር 27

1 እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፤
የሚያስፈራኝ ማን ነው? እግዚአብሔር የሕይወቴ
መታመኛዋ ነው፤ የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?
2 ክፉዎች፥ አስጨናቂዎቼ ጠላቶቼም፥ ሥጋዬን
ይበሉ ዘንድ በቀረቡ ጊዜ፥ እነርሱ ተሰናከሉና ወደቁ።
3 ሠራዊትም ቢሰፍርብኝ ልቤ አይፈራም፤ ሰልፍም
ቢነሣብኝ በዚህ እተማመናለሁ።
4 እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት
እርስዋንም እሻለሁ፤ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ
በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፥ እግዚአብሔርን
ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ፥ መቅደሱንም
እመለከት ዘንድ።
5 በመከራዬ ቀን በድንኳኑ ሰውሮኛልና፥
በድንኳኑም መሸሸጊያ ሸሽጎኛልና፥ በዓለት ላይ ከፍ
ከፍ አድርጎኛልና።
6 እነሆ፥ አሁን በዙሪያ ባሉ በጠላቶቼ ላይ ራሴን
ከፍ ከፍ አደረገ፤ በድንኳኑም የእልልታ መሥዋዕትን
ሠዋሁ፥ ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ እዘምርለትማለሁ።
7 አቤቱ፥ ወደ አንተ የጮኽሁትን ቃሌን ስማኝ።
ማረኝና አድምጠኝ።
8 አንተ ፊቴን እሹት ባልህ ጊዜ። አቤቱ፥ ፊትህን
እሻለሁ ልቤ አንተን አለ።
9 ፊትህን ከእኔ አትሰውር፥ ተቈጥተህ ከባሪያህ ፈቀቅ
አትበል፤ ረዳት ሁነኝ፥ አትጣለኝም፥ የመድኃኒቴም
አምላክ ሆይ፥ አትተውኝ።
10 አባቴና እናቴ ትተውኛልና፥ እግዚአብሔር ግን
ተቀበለኝ።
11 አቤቱ፥ መንገድህን አስተምረኝ፥ ስለ ጠላቶቼም
በቀና መንገድ ምራኝ።
12 የሐሰት ምስክሮችና ዓመፀኞች ተነሥተውብኛልና
ለጠላቶቼ ፈቃድ አትስጠኝ።
13 የእግዚአብሔርን ቸርነት በሕያዋን ምድር አይ
ዘንድ አምናለሁ።
14 እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፤ በርታ፥ ልብህም
ይጽና፤ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።

## የዳዊት መዝሙር 91

1 በልዑል መጠጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ
ጥላ ውስጥ ያድራል።
2 እግዚአብሔርን። አንተ መታመኛዬ ነህ እለዋለሁ፤
አምላኬና መሸሸጊያዬ ነው፥ በእርሱም እታመናለሁ።
3 እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ ከሚያስደነግጥም ነገር ያድንሃልና።
4 በላባዎቹ ይጋርድሃል፥ በክንፎቹም በታች
ትተማመናለህ፤ እውነት እንደ ጋሻ ይከብብሃል።
5 ከሌሊት ግርማ፥ በቀን ከሚበርር ፍላጻ፥
6 በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር፥ ከአደጋና ከቀትር ጋኔን
አትፈራም።
7 በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ፤
ወደ አንተ ግን አይቀርብም።
8 በዓይኖችህ ብቻ ትመለከታለህ፥ የኃጥኣንንም ብድራት
ታያለህ።
9 አቤቱ፥ አንተ ተስፋዬ ነህና፤ ልዑልን መጠጊያህ አደረግህ።
10 ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፥ መቅሠፍትም
ወደ ቤትህ አይገባም።
11 በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ
ያዝዛቸዋልና፤
12 እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል።
13 በተኵላና በእባብ ላይ ትጫማለህ፤ አንበሳውንና ዘንዶውን
ትረግጣለህ።
14 በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ፤ ስሜንም አውቆአልና
እጋርደዋለሁ።
15 ይጠራኛል እመልስለትማለሁ፥ በመከራውም ጊዜ
ከእርሱ ጋራ እሆናለሁ፤ አድነዋለሁ አከብረውማለሁ።
16 ረጅምን ዕድሜ አጠግበዋለሁ፥ ማዳኔንም አሳየዋለሁ።

## የዳዊት መዝሙር 23

1 እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።
2 በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።
3 ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።
4 በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና
ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።
5 በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት
ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው።
6 ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ
ይከተሉኛል፥ በእግዚአሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።

አዘጋጅ ሊ/ኅ ቀሲስ ይስሐቅ ወልደ ማርያም

ጥያቄ ካላችሁ በ(703) 606-1976 ደውላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ።